የሰ/መ/ቁ. 139138

ህዳር 20 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋዬ አስማማው

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጸውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ኃይሉ ሂንጌ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አመርቲ ነሼ የፊንጫኣ ሀይል ማመንጫ ፕሮጀክት ነገረ ፈጅ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የክርክሩ መነሻ በጉዳት ካሳ ክርክር ላይ ተሳታፊ ለመሆን የቀረበ ነው፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የአሁን አመልካችን ጨምሮ አራት ከሳሾች የአሁን ተጠሪ ይዞታቸውን ለኤሌክትሪክ ማመንጫ ስለወሰደባቸው የንብረት ጉዳት ካሳ እንዲከፍል ክስ አቅርበው ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 14442 በቀን 28/6/2006 ዓም የሰጠውን ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሥር ከሳሾች መካከል የአሁኑን አመልካች ጨምሮ ሶስቱ ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ምድብ ችሎት አቅርበው ሲፀናባቸው ከይግባኝ ባዮች መካከል አቶ አመንቴ ደበሎ እና አቶ በላይ በየነ የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሲያቀርቡ የአሁን አመልካች ተሳታፊ አልነበሩም፡፡ የተጠቀሱት ሁለቱ አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ በሰበር መዝገብ ቁጥር 111629 የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሊጣሩ የሚገባቸውን ነጥቦችን በመለየት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት ለሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ መልሶታል፡፡

ጉዳዩ ከተመለሰ በኃላ የአሁኑ አመልካች በነጥብ የተመለሰው ጉዳይ እሳቸውንም የሚመለከት በመሆኑ ወደ ክርክሩ ለመግባት ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት ሲያመለክቱ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ የተሻረው ሁለቱን ከሳሾች በሚመለከት በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ አመልካችን አይመለከታቸውም ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ይህን ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ምድብ ችሎት አቅርበው ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመውብኛል ያሏቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ የአሁን አመልካች ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን በተጠሪ ላይ የካሳ ጥያቄ አቅርበው እስከ መጨረሻ ድረስ ተከራክረው ክርክራቸው ተቀባይነት በማጣቱ ከነሱ ጋር ተከራካሪ የነበሩ ሰዎች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበው በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት ተገቢው ማጣራት ተደርጎ እንዲወሰን በመመለሱ የአሁን አመልካች በተመለሰው ነጥብ መሠረት ለመከራከር የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለውን ለማጣራት ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብለናል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ተጠሪን በአድራሻ ለውጥ ምክንያት ለማግኘት ያለመቻላቸውን ገልጸው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ በጠየቁት መሠረት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ባለመቅረቡ ምክንያት መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ተደርጓል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አስቀድሞ እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ደርሶ በነጥብ በተመለሰው ጉዳይ የአሁኑን አመልካችን ጨምሮ አራት ሰዎች በአንድ ላይ ሆነው እያንዳንዳቸው የሚገባቸውን የንብረት ጉዳት ካሳ ግምት በማቅረብ በሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.14442 በሆነው ተከራክረዋል፡፡ ክስ ያቀረቡት በአንድ መዝገብ፣በአንድ ዓይነት ጉዳይ፣ በአንድ ላይ ነው፡፡ ይህም የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት

ህግ ቁጥር 35 ድንጋጌን የተከተለ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ክስ አቅርበው ከተፈረደባቸው ሰዎች መካከል አንዱ ይግባኝ አቅርቦ ውሳኔው ከተሻረ ወይም ከተለወጠ ወይም ከተሻሻለ ይግባኝ ያልጠየቀው ሰው የፍርዱ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 331 በአንድ ክርክር ውስጥ የከሳሾች ወይም የተከሳሾች ብዛት ከአንድ በላይ ሲሆንና ክርክሩም ከሳሾችን ወይም ተከሳሾችን በአንድ ዓይነት መልክ የሚመለከታቸው ሲሆን ከሳሾቹ ወይም ከተከሳሾቹ አንዱ በጠቅላላው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ በዚህ ዓይነት ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደነገሩ አከባቢ ፍርዱን በማሻሻል ወይም በመለወጥ ያሻሻለው ወይም የለወጠው ወይም ያጸናው ፍርድ ይግባኙን ባላቀረቡት ከሳሾች ወይም ተከሳሾች ላይም ይፀናባቸዋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 35 ላይ የተደነገጉትን ዝርዝር ነገሮችን ባሟላ መልኩ በአንድነት ሆነው ክስ ያቀረቡ ከሳሾች ከውሳኔ መልስ በይግባኝ ደረጃም በቀረበው ጉዳዩ ከከሳሾቹ መካከል አንዱ ይግባኝ ጠይቆ የሚሰጠው ውሳኔ ሌሎችንም እንደሚያካትት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለጸው የአሁኑን አመልካች ጨምሮ አራት ከሳሾች ክስ መስርተው በአንድ መዝገብ የተከራከሩ ናቸው፡፡ ጉዳዩ ንብረት ካሳን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እያንዳንዱ ከሳሽ ለራሱ የሚገባውን የካሳ መጠን ገምቶ ማቅረብ ማለት ግን ለየብቻው ክስ አቅርቧል ሊያስብል አይችልም፡፡ የሆሮ ጉድሮ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ሲያደርግ በትዕዛዙ ላይ የገለጸው ምንም እንኳን ከሳሾቹ በአንድ ላይ ክስ ቢያቀርቡም እያንዳንዳቸው የካሳውን መጠን ለይተው ያቀረቡ ስለሆነ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በነጥብ በተመለሰው ጉዳይ አመልካች ሊከራከሩ አይችሉም የሚል ሲሆን ይህም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 35 እና 331 ድንጋጌን መንፈስና ዓላማ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.14442 በቀን 07/10/2008 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.209044 በቀን 13/04/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ወደ ክርክሩ ውስጥ ገብተው ለመከራከር ያቀረቡት አቤቱታ የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 331 ድንጋጌን የተከተለ በመሆኑ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 111629 ላይ የሚጣሩ ነጥቦች ተይዘው በተመለሱት መሠረት በመ/ቁ. 14442 በሆነው ላይ የአመልካች ክርክር ቀጥሎ ፍርድ ቤቱ አከራክሮ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በተመለሰው መሠረት የሁለቱ ከሳሾች ክርክር ውሳኔ አግኝቶ ከሆነም የአመልካች ክርክር በዚያው መዝገብ ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ ይገባል ብለናል፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይደረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ